# ተስፋዬ ገብረአብን የተካው የኢሳቱ ባንዳው ኤርምያስ ለገሰ ስለ ኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ምን እያለ ነው?

ጌታቸው ረዳ ኢትዮጵያን ሰማይ አዘጋጅ Getachew Reda(Editor Ethiopian Semay)



እንደምን ሰነበታችሁ። የምንወያየው ስለ የወያኔ ሚኒስቴር የነበረ ዛሬ ደግሞ የኢሳት የፖለቲካ ተንታኝ የሆነው ስለ ኤርሚያስ ለገሰ ነው። ተቃዋሚው ጎራ የህዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ "ፋሺስቶች" እጅ እና እግር ሆነው የሕዝባችንን መከራ እንዲራዘም ከፍተኛ ባንዳዊ ሥራ በመስራት ሲያገለግሉ በነበሩ አፍረተ-ቢስ ግለሰቦች የተሞላ ከመሆኑ ባሻገር፤ የዜና እና የትንታኔ መደብሮችን "ሚዲያዎች" በዋና ተንታኝነትና አዘጋጅነት ተቆጣጥረው "ላደረሱት በደልና ቅጥረኛነታቸው፤ ይቅርታ ሳይጠይቁ" ሓፍረት ምን ማለት እንደሆነ በማያውቅ አንደበታቸው ዛሬም የኢትዮጵያን ክብር ከሚጻረሩ ቡድኖች ጋር በመሆን፤ ወያኔ ጎራ ሆነው የለመዱትን የኢትዮጵያን ክብር የሚያዋርድ ድፍረታቸውን በሚዲያ ሲረጩ እያደመጥን ነው።

የኤርትራ ጉዳይ ሲነሳ ግምባር ቀደም የሻዕቢያ ፕሮፓጋንዳ ደጋፊዎች ሆነው ብዙ ብከላ ሲበክሉ የሰማናቸው እነ ዳዊት ወ/ጊዮርጊስ፤ ካሳ ከበደ (ኢሳትና ግንቦት 7 ቡድን በጠቅላላ) ሳያንሰን ዛሬ ደግሞ ከወያኔ ጉያ ሸሽቶ ወደ ውጭ አገር በመሰደድ፤ ከእኩያዎቹ ጋር በመሆን (ሙሉጌታ ሉሌ፤ ሲሳይ አገና ጋር ሆኖ የተወያው) የ1991-2000 የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት የቆመበት ምክንያት ጓደኛው የኢሳቱ ሲሳይ አገና አምና እንደገለጸው "ዛሬም ሻዕቢያ ከወያኔ/ኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት የበረታ እና የማይበገር" መሆኑን መረጃዎች አሉኝ እንዳለን ሁሉ፤ ኤርሚያስ ለገሰም "የባድመ ጦርነት" በሻዕቢያ ተዋጊዎች ተገፍቶ እንደቆመና ኢትዮጵያ ተዋጊዎች ሻዕቢያን ሃይል መቋቋም ስላልቻሉ መሆኑን ታሪክ መመዝገብ አለበት ይለናል። ለዚህ ሻዕቢያዊ ፕሮፓጋንዳው ደግሞ ታሪክ እንዲዘግበው ታሪክን ይጠይቃል። ዝርዝሩን በሰፊው ወደ ታች አቀርባለሁ፤ ለመግቢያ እንዲሆናችሁ ይሄው
እንዲህ ይላል።

"ታሪክ ስለሆነ ነው፤ የታሪክ ጥያቄም ስለሆ ነው። ታሪክ ያወጣዋል የምልህም "እውነት ስለሆነ ነው"፡ **ይኼ እውነት ነው"።** ሲል ባንዳው ኤርትራዊው መለስ ዜናዊ ስብሰባ ላይ "ጦርነቱ የቆመበት ምክንያት የተናገረው **እውነታ ስለሆነ"** ፤ ኤርምያስ ምስክርነቱን በመለስ ማስረጃ ተንተርሶ ሲፏክት እንመለከታለን።

መለስ ይህንን በሚመለከት እንኳን እንደ ማስረጃ ለምስክርነት ሊበቃ ቀርቶ ጦርነቱ እንኳ “ኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት የተመራበት መንገድ “የኪራይ ሰብሳቢነት ነው” ሲል ነበር ስም የሰጠው። እንዲህ ያለ መሪ ነው ኤርሚያስ እንደማስረጃ ለታሪክ አቅርቦ ኢትዮጵያዊያኖች እንደተሸነፍን አስመስሎ ሲዋሽ ውሸቴን አድምጡኝ፤ታሪክ ይመዝግብልኝ እያለን ያለው።

ባንዳነትና ጎሰኛነት እስከመቸም የማይለቅ በሽታ እንደሆነ ካሁን በፊት ገልጫለሁ። እንኚህ የተበከሉ ናቸው። የተበከለ ነገር ተሎ ኣይለቅም። ለዚህም ነው ሳት ብሎ የፖለቲካ አካሄዳቸው እና ከነማን አንደሚተሻሹ “የሚያገረሽ ጠረናቸው እያስቸገረን ያለው”። ስለሆነም ኤርሚያስ በማያውቀው ጉዳይ ገብቶ ለሻዕቢያ አገልግሎት የሚውል ፕሮፓጋንዳ ሲሰራ አድምጫለሁ። (ለምን? ኢሳት የሻዕቢያ ገንዘብ እና ቁሳዊ ዕርዳታ ያስፈልገዋልና ነው።አንዳርጋቸው አድርጎታል፤ ንአምን አድርጎታል፤ ብርሃኑ ነጋ አድርጎታል፤ኤፍሬም ማዴቦ፤ፋሲል የኔ አለም፤ መሳይ ... አድርገውታል.... የባንዳዎች መብዛት ቢያስገርም እንጂ ባንዳ ብቅ የማለቱን አዲስ አልሆነንም። )

ኢትዮጵያዊያንም ሃቁን ታሪክ እንዴት እንደዘገበው በበኩላችን የእነ ኤርሚያስ ለገሰ ቅጥረኝነት ለማፍረስ ሃላፊነት ስላለን ታሪክ እንዴት እንደዘገበው በራሳቸው በኤርትራ መሪዎች ጦርነቱን በመሩት ከፍተኛ ባለሥልጣኖች አንደበት ከኤርምያስ ለገሰ ጋር እያነጻጸርኩ ታሪክ በመዝገቡ እንዲይዝልን አቀርብላችኋለሁ። ቾል እያልን ብዙ ተጃጅለናል። ክፍት ቦታ መስጠት ባንዳዎችን ያበረታታል፤ አለፍ ብሎ የሚያገረ ጠረናቸው ታሪክን ይበክላል። እንጋፈጣቸው።

ይህ ግለሰብ እጅግ፤እጅግ አደገኛነቱን የምትረዱት ልክ እንደተስፋዬ ገብረአብ ነገሮችን በመጽሐፍ መልክ የመተንተን ችሎታ ስላለው፤ ብዙ ሰዎች ሊያጃጅል የሚችል ነው። ግን ቀረብ ብሎ ለተከታተለው ሰው እውነት የሚሸሽ አጭበርባሪ ነው። አጭበርባሪነቱንም ለማረጋገጥ አንድ ምሳሌ ልስጥ እና ወደ ርዕሴ ልሸጋገር። አብረውት ከወያኔ ጋር ሲያገልግሉ ለነበሩት እና አሁንም እዛው በማገልገል ላይ ላሉ ባንዳዎች መልዕክት ሲያስተላልፍ “ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ይቅርታ መጠየቅ አለባችሁ” ሲል እራሱ አንድ ቀን እንኳ ይህንን በሚመለከት ሕዝብ ለስብሰባ ጠርቶ ለታሪክ ምዝገባ ብሎ ይቅርታ የሚጠይቅበት ራሱን የቻለ አጀንዳ/ውይይት አላዘጋጀም። “የወያኔ ውላጅ ነበርኩ” ከማለት በቀር በጨረፍታ እንኳ ከወያኔ ጋር ሆኖ ሲያደርጋቸው የነበሩትን አስጸያፊ አግልግሎቶቹ አንስቶ ይቅርታ አልጠየቀም። ግን እንዳልኳችሁ የተቃዋሚ ሚዲያዎቹ “በባንዳ ነበሮች” የተወረረ ስለሆነ፤አብረው ወያኔ ሲያገለግሉ ይተዋወቁ ስለነበር “አይጨካከኑምለ ፤ ይደጋገፋሉ”፡ ሕዝቡም አንጨብጫቢ ስለሆነ፤ በሕዝብ ሕሊና ማሾፋቸውን ቀጥለውበታል።

ይህ ሰው በዲያቆን ዳንኤል ክብረትና በጋዜጠኛ ተመስገን ደሳለኝተተችቷል።

ዳኔኤል ከብረት ኤርሚያስ ለገሰ ስለ ጸረ ማራነት እና ስለ አክራሪ እስላሞችን አስመልከቶ ፤እራሱ ኤርምያስ ለገሰ ለቤተክርስትያን የነበረው ወያኔአዊ ባሕሪው እንዲህ ሲል ይተቸዋል፤-

“ኤርሚያስ ኤርሚያስ ሆይ! አንተ ዛሬ ስትወጣ በሌሎች ብቻ አመካኘኸው እንጂ በአዲስ አበባ አየር ጤና ኪዳነ ምሕረት የጥምቀት ቦታ ክርክር ጊዜ የመንግሥትን ሥልጣን ይጠቀሙ ከነበሩት ሰዎች አንዱ ነበርክ፡፡ በወቅቱ እኔ የማኅበረ ቅዱሳን ሚዲያዎች ኃላፊ ነበርኩ፡፡ ጉዳዩን ከእግር እስከ ራሱ ዐውቀው፣ እከታተለውም ነበር፡፡ መረጃዎቹንም ከየአቅጣጫው እናገኝ ነበር፡፡ አጠናቅረንም በጋዜጣ እናወጣ ነበር፡፡ በዚያም ምክንያት አያሌ ጫናዎችን ካደረሱብን ሰዎች አንዱ አንተ ነበርክ፡፡ ቢሮህ አስጠርተህን ቤተ ክርስቲያኒቱንና የፈረደበትን አማራ ምን ብለህ እንደተሳደብክ  የምናውቀው አንተ እና እኛ ነን፡፡”

በበሻሻ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያን ጅማ ውስጥ በጥቅምት 1998 ዓም አክራሪ ሙስሊሞች በየዋሐን ምእመናንና ካህናት ላይ የፈጸሙትን ግድያ ሕዝቡ ሲሰማኮ አንተና ሌሎቻችሁም ጣታችሁን እኛ ላይ ጠቁማችሁ ስንት ቀን እሥር ቤት አመላልሳችሁናል፡፡ አንተ ራስህ በመጽሐፍህ የገለጥከው ራስህ ቆመህ ያስፈረስከውን ቤተ ክርስቲያን በተመለከተ በድፍረት መጀመሪያ የዘገብነው በስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ ላይ ነበር፡፡ ያኔ ምን እንዳላችሁን ታውቃለህ፡፡” **ዲ/ን ዳንኤል ክብረት ለአቶ ኤርሚያስ ለገሰ የሰጠው ምላሽ: ኤርምያስ ኤርምያስ ሆይ!**
http://www.satenaw.com/amharic/archives/5106

ኤርምያስ ለገሰ ዛሬም ስለ ኤርትራኖች ወግኖ ታሪክ እያጣመመ ሕዝብን በመበከል ላይ ይገኛል። አዎ! ኤርትራ እነ ተስፋዬ ገብረአብ እነ ኤርሚያስ ለገሰ አሉዋት (በነገራችን ላይ እንደሰማሁት እውነት ከሆነ ኤርሚያስ ‘ኦሮሞ’ ነኝ ይበል እንጂ ‘ኤርትራ” እንደሆነ ነው ከሰዎች የሰማሁት፤ባንድ ፓልቶክ ሲነገር የነበረው ዘርዝሩ ሰፊ ነበር። “እወነት ነው”? አላውቅም። ሆነም አልሆነም፤ ለኤርትራ ያደሩ ብዙ ኦሮሞዎች ስላሉ አይገርምኝም) ፤ ኢትዮትዮጵያ ደግሞ እኛ ልጆቿ ስላለን እውነታውን እንመዘግባለን።

በኤርሚያስ ለገሰ ንግግር እንጀምር። ፕሮፓንዳው ኤርትራኖች ስለወደዱት ቪዲዮው ‘ዩ ቱብ’ ውስጥ “በኤርትራኖች” የተለጠፈ ነው። ርዕሱ እና አድራሻው እንዲህ ይላል፡- Who wins the Ethio - Eitrea war 1998 - 2000 https://youtu.be/Gei2sSzeeMM

ኤርሚያስ እንዲህ ይላል። እነሆ!

“ምናልባት ታሪክም ያወጠዋል እምለው ምንድ ነው፤...በወቅቱ እማስታውሰው ነገር፤ በኢትዮ- ኤርትራ ጦርነት ጊዜ፡- አንዳኛ፡- **እውነት ኢትዮጵያ አሸንፋ ነው ወይ ጦርነቱ የቆመው?** የሚለው ጥያቄ **“ሲርየስ” ጥያቄ** ነው። **የታሪክ ጥያቄ ስለሆነ** ማለት ነው። ከትግራይ የመጡ ካድሬዎች፤የወረዳ ...የመጡ ካድሬዎች ፤በባድሜ ላይ የነበራቸው ስሜት ከፍተኛ ነው። ጦርነቱ በመቆሙ ቅሬታ አላቸው። ህወሓትም “ቤዚካሊ” ለሁለት የተከፈለው የጦርነቱ መንስኤ የመስለኛል። “ኦልሞስት” በተለይ የወጡት ሰዎች ያንን ነው የሚያነሱት።በተለይ ከትግራይ የመጡ ካድሬዎች ጦርነቱን ገፍተን መሄድ እንችል ነበር፡ (እንዳይቀጥል ያደረጋችሁ) መለስ እና የመለስ ቡድኖች ናችሁ ጦርነቱ እንዲቆም ያደረጋችሁ፤የሚል በጣም አደገኛ

ውይይት ነበር።ከማልረሳቸው ውይይቶች አንዱ ይኼ ነበር። በኋላ ይኼ ወሬ (መለስ) ይደርሰዋል።...... (መለስ) ኢትዮ-ኤርትራ የተመራበት መንገድ “የኪራይ ሰብሳቢነት ነው” የሚል ነው ለማስጨበጥ የፈለገው አቶ መለስ። በኋላ (የሚያነሱት።በተለይ ከትግራይ የመጡ ካድሬዎች ጦርነቱን ገፍተን መሄድ እንችል ነበር፡ (እንዳይቀጥል ያደረጋችሁ) መለስ እና የመለስ ቡድኖች ናችሁ ጦርነቱ እንዲቆም ያደረጋችሁ) መለስ ይህንን ሲሰማ በጣም “አፈንድድ” ሆኖ <u>**“ጦርነቱ የቆመው ስላሸነፍን ሳይሆን በራሱ ጊዜ ተንገራግጮ ነው የቆመው!”**</u> ። አላቸው። ይህች ናት ቃሉ <u>**ተንገራግጮ ነው የቆመው!**</u>” ይህች ናት ቃሉ። “<u>**ተንገራግጮ ነው የቆመው!**</u>”

“ተንገራግጮ የቆመው ደግሞ በሦስቱ ግምባሮች የነበሩ ጀኔራሎች፤ (ታስታውስ እንደሆነ የባድሜ፤ዛላምበሳ፤የቡሬ ግምባር) በሦስቱ ግምባሮች የነበሩ ጀኔራሎች በተናጠል ስናነጋግራቸው፤ ለምሳሌ በባድሜ ግምባር የነበረው ጀኔራል ያለን ነገር በኛ በኩል መግባት ኣይቻልም፤ እምትችሉ ከሆነ በቡሬ እና በዛላምበሳ ግቡ አለን። የቡሬውን ስናነጋግረው ደግሞ በቡሬ በኩል ኣይቻልም፤ እሚቻለው በሁለቱም ጋር ነው። ስለዚህ ሦስቱም በተናጠል መረጃ ስጡ ሲባሉ በራሳቸው በኩል እንደማይቻል እና በሌላ በኩል እንዲሞከር ነው “አድቫይስ” የሰጡት ማለት ነው። This is what he said. አሁን ደግሞ የገብሩ አስራት መጽሐፍ አይተህ ከሆነ <u>**“እኔ እንግዲህ ታሪክ ይፍረድ ያልኩህ ለዚያ ነው”**</u> ገብሩ አስራት መጽሐፍ ደግሞ ምን ይላል፤ “ሁለቱ ጀኔራሎች እምቢ አሉ፤ ነገር ግን እምቢ እንዳሉ ሲያውቅ፤ ሳሞራ የሚመራው ግምባር ደግሞ እሺ ኣለ፤ እንችላለን አለ” ይላል። አየህ! እንግዲህ ይኼ ነው በመሃል ያለው ነገር። ዞሮ ዞሮ፤ ግን በሁለቱ ጦር ግምባር የነበሩ ጀኔራሎች ጦርነቱን ገፍቶ መሄድ አይቻልም” የሚል ኮንኩሊዥን/መደምደሚያ/ ነበር።”

<u>***ሲሳይ አገና፡***</u>
ስለዚህ በዛም አለ በዛ መግፋት ስላልቻልን ነው።
<u>**ኤርሚያስ ለገሰ፡**</u> አዎ።ጦርነቱ ስላልገፋ የሚል ኮንኩሉዥን ነው፤ “ኢቨን” የገብሩ መጽሐፍም ሳሞራ ያለበት ምክንያት እነሱን ከሰማ በኋላ “ሳሞራ መግፋት እንችላለን” ያለበት ምክንያት ሳሞራ ከመለስ ጋር ስለሚጣበቅ፤መለስ ከበስተጀርባ የሆነ ነገር ስላለው ነው የሚል ነው......ተረዳኸው ፖለቲካው? ከጀርባ ያለው ፖለቲካው ማለት ነው።ስለዚህ ታሪክ ያወጠዋል የምለው <u>ይሄ እውነት</u> ነው። አንዱ <u>እውነት</u>።

‘እና ኢህዴግ ፤የኢትዮጵያ መንግሥትም ጎበዝ ከሆነ ያንን ቪዲዮ ይልቀቀው።<u>**እኛ**</u> የምንናገረው ሃሰት ከሆነ።

<u>**ሁለተኛው**</u> ጀኔራሉ ያለውን “ዊኪሊኪ” ያወጣው ነው። አንተ ቅድም ያልከው።

<u>**ሦስተኛው**</u> አየር ሃይሉ ነው። ጋሽ ሙሉጌታ (ሟቹ የኢሳት ዋናው ሰው የነበሩት ሙሉጌታ ሉሌ ማለቱ ነው) የሚያነሱት ማለት ነው ። አሁንም ታሪክ የሚያወጣው በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ፓይለቶቹ የድሮ አየር ሃይል ፓይለቶች ናቸው ሌሎች ፓይለቶች አልነበሩም። እነዛም

*ፓይለቶች የተወሰኑት ተመትተው ነው የነበረው። በተለይ መቀሌ ላይ የኤርትራ ፓይለቶች መጥው መቀሌ ውስጥ መጥተው የተወሰኑት ተመትተዋል፤የቀሩትም ቢሆን በዛብህ ጴጥሮስ ኤርትራ ሄዶ፤ ኤርትራ (ውስጥ ) ተመታ፤ አንደኛው ደግሞ ወደ ኢትዮጵያ ሲመለስ የራሱን (አይሮፕላኖች?) መትቶ "**ጨፈረ**" ። **አይሮፕላን አብራሪም የለም**፡ በሌለበት ሁኔታ ነው ያለው እና* that is why I think *ወደ ስምምነትም የገቡት "በአየሮፕላን የመመታታት ይቁም" የሚለው የተስማሙት።"*

*(**ይሮፕላን አብራሪም የለም**፡ ባጣም አስገራሚ ፕሮፓጋንዳ!!!! አዬ ኤርሚያስ! በዚህ አየር ሃይል በኩል ራሱን የቻለ በሌላ ጊዜ እመለስበታለሁ። ቪዲዮዎች የተደገፉ መረጃዎች አሉኝ። የኤርትራ አይሮፕላኖች ከመብረር ታግደው የት ተደብቀው እንደነበር፤ ሌላ ቀን እመለስበታለሁ። 'መቀሌ ተቆጣጥረናል ሽሬ ይዘናል፤አዲስ አበባ እንገሰግሳለን 'የያኔው ፕሮፓጋንዳ የኤፍሬም ለገሰ ትንሽ ሕሊና አምታትቶታል። አየህ ኤርሚያስ! ሓፍርተ የት ነው አገሩ?! ) የመቀሌ ገርገምበስ አየር ማረፊያ ካምፕ ትቶ የትምህርት ቤት ህጻናት የፍጀበትን ነው፤"መቀሌ ውስጥ መጥተው የተወሰኑት ተመትተዋል" ኢያለን ያለው።*

"በተለይ መቀሌ ላይ የኤርትራ ፓይለቶች መጥተው መቀሌ ውስጥ መጥተው የተወሰኑት ተመትተዋል፤የቀሩትም ቢሆን በዛብህ ጴጥሮስ ኤርትራ ሄዶ፤ ኤርትራ (ውስጥ ) ተመታ፤ አንደኛው ደግሞ ወደ ኢትዮጵያ ሲመለስ የራሱን (አይሮፕላኖች?) መትቶ "**ጨፈረ**" ። **አይሮፕላን አብራሪም የለም**።በሌለበት ሁኔታ ነው ያለው እና that is why I think ወደ ስምምነትም የገቡት "በአየሮፕላን የመመታታት ይቁም" የሚለው የተስማሙት።"

ሲል ኢሳት ውስጥ ተስፋዬ ገብረአብን የተካው ኤርሚያስ ለገሰ ኢትዮጵያዊያን በሻዕቢያ/ኤርትራዊያን ስለተሸነፉ ነው ጦርነቱን መግፋት ያልቻሉት ሲል የኢትዮጵያዊያንን ሃያል ክንድ እራሳቸው የሻዕቢያ መሪዎች እና ዓለም የመሰከረውን ውግያ 'ተወጊዎቻቸው ብረታቸውን እየጣሉ ወደ ሱዳን በየ አቅጣጫው ነብስ አውጪ እንደፈረጠጡ፤ ¾ የኤርትራ ሰፊ መሬት በኢትዮጵያዊያን ቁጥጥር እንደነበር ወደ አስመራ ሊዘልቁ ሲሉ፤ ጀኔራሎቹ ሳይውቁና ባልተስማሙበት ድንገት "መለስ እንዳስቆማቸው" ተዋጊዎቹና አዋጊዎች እንዴት እንደተገረሙ እናስታውሳለን። ከፍርሃት የተነሳ **"ኢሳያስ አፈወርቂ"** የስላላና መንግሥታዊ ፋይሎችን፤ምስጢሮችን የያዙ መዛግብቶች በሙሉ ግማሹ ተቃጥሎ ግማሹ በግመል ወደ ናቅፋ እንዲጓጓዝ ሲደረግ፤ ድንግት መሰል ጦርነቱን ማስቆሙ ሲሰማ፤ ግመሎቹ እንዲቆዩ እና ሁሉንም በየቦታው እንዲመለስ መደረጉ የራሳቸው ሰዎች **"ስመር"** በታበለ የኤርትራኖች "ፓልቶክ" አምና ነግረውናል። አውዲዮውም በእጄ አለ

ኢሳያስ ብርክ ይዞት አስመራ እንደሚገቡ ጠርጥሮ ስለነበር በፍርሃት ተውጦ ሲናገራቸው የበሩትን ንግግሮች የቅርብ ሰዎች በየፓልቶኩ የተናገሩትን አድምጠናል። ጦርነቱ እንዲያስቆምላቸው "የአድኑን" ተማጽኖ ለፕረዚዳንት ክሊንተን እና ለተባበሩት መንግሥታት ምን ብሎ ደብዳቤ እንደጻፈ፤ ጦርነቱ ወዶ ሳይሆን ተምበርክኮ 25 ኪ/ሜ ርቆ እንዲቆይ ለምን እሺ ብሎ እንደፈረመ "እባካችሁ ጦርነቱን አቁሙልን፡ እያለ የተማጸነውን ሁላችንም

የምናውቀው የቅርብ ታሪክ ነው። ተዋጊዎቹ በየሱዳን እና የመን እየፈረጠጡ በያቅጣጫው እንዴት እንደሸሹ፤ እናውቃለን። ባረንቱ ሁሉ ኢትዮጵያዊያን ገብተው ተቆጣጥረውታል። አሸናፊ እንጂ ተሸናፊ ይህ ሁሉ መሬት ዘልቆ እንዴት ሊይዝ ቻለ? ኤርሚያስ ንገርን እንጂ?! አስመራን የሚያውቅ ከባረንቱ ከሰራዬ፤ ዓዲ ቐይህ ተራሮች፤ ከአከሎግዛይ/አምባሶይራ እና ከዓይጋ ተራሮች ወዲያ አስመራ ለመግባት ምን የሚሉት ስትራተጂ የመዋጊያና መከለከያ ተራራ አለ? በቀጥታ ነው የምትቆጣጠረው።

ብዙ የቪዲዮ እና የአውዲዮ ቃለ መጠይቆች በራሳቸው ተዋጊዎች የመሰከሩትን ምስክርነት በየፓልቶኩ ተለጥፈዋል።መረጃዎች እንደ አሸን ሞልተዋል። በዚህ ረገድ ሌሎቹን ተራ ተዋጊዎቹን የሰጡዋቸውን ምስክሮች ለጊዜው እናቆይ እና ከፍተኛ የሻዕቢያ መሪዎችና የውግያ ተንታኞች ከነበሩት የድሮ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር (ከወያኔ ጋር ኦጎድጉ እና አልጀሪስ ሲደራደር የነበረው) ኤርትራዊው የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የነበረው ሃይለ ድሩዕ <u>“ወያኔ አጣላቕየሙና እዮም”</u> (ወያኔዎች ድባቅ መቱን/ አንቀጠቀጡን/ አሸኑን/ላብ-በላብ አደረጉን፤ውስጥ ባሕር ውስጥ እንድንሰምጥ ደፈጠጡን/አሰመጡን....እንደማለት ይመስለኛል ወደ አማርኛ ሲተረጎም፤ ትግርኛው እጅግ ከዚህ በከፋ የሚተረጎም ነው፤ አማርኛው ለስለስ ይላል)።

ሃይለ ድሩዕ ጀርመን ውስጥ ኤርትራ ፈስቲቫል ተገኝቶ “ባጭር ጊዜ እና ባስገራሚ ሁኔታ እንዴት ኢትዮጵያዊያን በፈንጅ የታጠሩ ረዢምና አስቸጋሪ ምሽጎችን ሰብረው የኤርትራኖችን እንዳሯሯጧቸው፤ “የተደረገው ሁኑታ ብንሸሽጋችሁ ነገ በታሪክ እንወቀሳለን፤ ለብዙ ጉዜ አሞኝተናችኋል፤ ዛሬ ግን ሃቁን ስንነገራችሁ መሸነፋችን እንደሚያማችሁ ቢገባኝም፤ የግድ ማወቅ አለባችሁ።” ብሎ ስለተናገረ እስር ቤት ገብቶ “ዓይኑ ታውሮ፡ የሱካር በሽተኛ ሆኖ ደብዛው ከጠፋ 16 አመት የሆነው “ሃይለ ዱሩዕ” (ሃይለ ወልደትንሳኤ) ሃቁን ነግሮናል። ሃይለ ዱሩዕ ማለት ከመግቢያ ጹሑፎ ላይ ከላይ እመሃል የሚታየው ፎቶ ግራፍ ነው።

እሱን በመደገፍና የመታሰሩን ሁኔታ በመቃወም፤ ኢንተርኔት ላይ በቪዲዮ ቀርጾ ሃቁን የነገረን ደግሞ ሌላው የሻዕቢያ ኮማንደር እና አምባሳደር የነበረው “አድሓኖም ገብረማርያም” (በግራ በኩል ያለው) ስለ ጦርነቱ እና ሃይሌ ወ/ተንሳይ እራሱ ጀርመን ውስጥ ኤርትራኖችን ሰብስቦ ስለተናገረው ምስክርነቱ ሲያብራራ ስለ ጦርነቱ እውነታውን እንዴት እንደነበር ደግሞ እንመልከት።

ባጭሩ <u>አድሓኖም ገብረማርያም</u>
በጋሽ ሰቲት በኩል የነበረው 8 ክ/ጦር በጥቂት ጊዜ እንዴት እንደፈረሰ እና ዓዲ ኳላ እና ዓረዛ፤ ሕዝብ እና ተዋጊ ሃይሎች ተበታትኖ አገሬ አውጪን እያለ እንዴት በየማዕዝኑ እንደፈረጠጠ ይነግረናል።

እንዲህ-ይላል፤

ወያኔዎች አምባሶይራ አምባዎች ላይ ጥርጊያ ጠርገው ታንኮች አምባሶይራ አምባዎች ላይ ነድተው ሰንደቃላማቸው ሲተክሉ ማየት የውርደት ውርደት ነው። ዓሰብ ትታችሁ ውጡ ተብሎ ነበር፤ የነበሩ ታንኮች ወደ ምጽዋ፤ዓሕላክ እንዲሸሹ ተደርጓል። ወታደሮች ያለ ታንክ እና ከባድ መሳርያዎች ዓሰብን እንዲከላከሉ ባዶ እጃቸው ክላሽ ይዘው ለጠላት እንዲጋለጡ ማድረግ ይህ በራሱ "ዕብዶች የሚያደርጉት ስትራተጂ ነው"። ዓሰብ ለቅቃችሁ ውጡ ማለት ለሉዓላዊነታችን ትልቅ ኪሳራ ነው። ዓሰብ መተው ማለት "በነጭ ሳህን ለአማራዎች ማስረከብ ማለት ነው፡" አንድ ሚሊዮን የሚሆን ሕዝብ ከወታደሮች ጋር ተደባልቆ ያለ ምንም አይዞህ ባይና ተከላካይ በየቦታው እየሸሸ አልተፈናቀለም፤አልተበተነም፤አልፈረሰም እንዴ? አልሸሸም? ይህ ሁሉ ወታደራዊ ውርደት እና ስንፍና አልገጠመንም እንዴ? በዚህ ወረራ ተሸንፈናል! ይህ ሁሉ ውርደት እንዴት እንገልጸዋለን? ከዚያም የከፋ ማለት ይቻላል።

"በዚህ ውግያ ተሸንፈናል። ማን እንሸሽ ፤ማን ደግሞ እንቀጥል ብሎ ስብሰባ ውስጥ እንደተናገረ ታሪክ ሊመዘግበው ነው። አልጄሪያ ሄደን፤25 ኪ.ሜ ከመሬታችን ርቀን ለባዕድ ሃይል አስረክበን ወደ ሗላ እንድንዘልቅ የተስማማነው ስለተሸንፍን ነው ወይስ ስላሸነፍን? ተምበርክኮ መፈረም ይህ የአሸናፊነት ምልክት ነው እንዴ? ወያኔዎች ከዚያ ካልራቁ ጦርነቱን እንደገፋብታለን፤መጣንባችሁ! ስላሉ ፤ ቢገፉ መቋቋም እንደማንችል ስላወቅን እነሱ በፈለጉት ተስማምተን 25 ከ/ሜ ራቅን! እውነታው ለምን እንደብቃለን? ሃይለ ድሩዕ ነፃነቱን አግኝቶ እዚህ አውጭ አገር አሁን ቢኖር ከዚህ በላይ ይነግረን ነበር። ስለ ተሸነፍን ጉልበት ስላጣን ኢትዮጵያዊያኖች ባቀረቡት አጀንዳ ተቀብለን ፈረምን። ወደን ሳይሆን ተምበርክከን ኢትዮጵያዊያን ባቀረቡት አጀንዳ አይደለም ወይ የፈረምነው? 25 ኪ.ሜትር መሬትክን ለባእድ አስረክበህ መስማማት፤ ለኤርትራዊ ማንነትና ሰውነት "ውርደት ነው"! በዚያ በሦስተኛው የወያኔ ወረራ ያልደነገጠ፤ ያልሰጋ፤ያላሳሳበው እውነተኛ ኤርትራዊ አልነበርም።"

ወያኔ እንዳለው የኤርትራ ሕዝብ አልተሸነፈም፤ የሻዕቢያ መንግሥት ግን እስኪበቃው አሸተነዋል እንዳለው። ልክ ነው ሕዝባችን አልተሸነፈም ይህ መንግሥትና አመራሩ ግን ተሸንፏል። ባድሜ የኤርትራ ነው ብሎ በሕግ ወስኗል። ጉልበት ስላላቸው ኢትዮጵያዊያኖች ጉልበት ስላለን ከባድሜ አንወጣም ምን ታመጡ! ብለው ንቀውን አሁንም ባድሜ በይዞታቸው ተቆጣጥረውት ይዘውታል። ይህ የመሸነፍ ምልክት አይደለም እንዴ? አሸናፊ መሬቱን ለዚህ ሁሉ አመታት አስረክቦ ዝም ይላል እንዴ፡ አሸንፈን ቢሆን ኖሮ? ይህ ሁሉ ሰው አስፈጅተህ ስታበቃ መሬትህ ተይዞ እንዴት ነው አልተሸነፍን ማለት የምንችለው? ካልተሸነፍን ለምን ባድሜ መያዝ አቃተን? እንዴት ማስመለስ አቃተን? እንቆቁሉሹን ንገሩን እንጂ! ባድሜ አንሰጥም! ኤርትራኖችን በውግያ አሸንፈናቸዋል እና ምን አባታቸው ሊያመጡ ነው? የት ሊደርሱ ነው እያሉ ነው የሚናገሩት። "አልተሸነፍንም አንፈራም፤ በዛው ጦርነት አልተሸነፍንም፤ አልሰጋንም፤ የሚል ካለ ሥልጣኑን ለማቆየት የሚባዝነው የሥርአቱ መሪና አሽቃባጮቹ ካልሆኑ በዛው ጦርነት ያልደነገጠ ኤርወትራዊ አለ ማለት ለማመን አስቸጋሪ ነው"

“ጦርነቱ በጥበብ በጥናት የተካሄደ አለነበረም፤ አዋጊ ሃላፊዎች የሚያውቁት ውጊያ አልነበረም፡ በዘፈቀደ ነበር ሲካሄድ የነበረው። ሰለሆነም ለውርደት እና ለሽንፈት ተዳረግን።”

በማለት ባጭር እና ግልጽ በሆነ በትግርኛ እንዲህ ሲል ደምድሞታል፡ “ዘጋጠመና ፖለቲካዊን ወታሃደራዊን ስዕረት ከቢድ እዩ ነይሩ” (በጦርነቱ ወቅት በኛ በኩል ኤርትራዊያን የገጠመን እና የታየው ፖለቲካዊ እና ወታደራዊ ሽንፈት ለመቀበል ለሕሊና የሚከብድ በጣም ከባድ ውርደት ነበር”። ሲል ደምድሞታል።

ዛሬ ግን የተስፋዬ ገብረአብን ሻዕቢያዊ ፕሮፓጋንዳ የሚያስተጋባው ተስፋዬ ገብረአብን የተካው የኢሳቱ ኤርሚያስ ለገሰ የሚለን ግን “ኢትዮጵያዊያን በኤርትራዊያን መሸናፈቸው **እውነት ነው”**። **የታሪክ ጥያቄ ነውና እውነት መሆኑንም ታሪክ መዘገብ አለበት** ይለናል፡ ከተመሳሳይ የሻዕቢያ ፕሮፓጋንዲስት ሚዲያ ከሚያካሂዱ ጓዶቹ ከኢሳት ሰዎች ጋር ሆኖ የተናገረው “ተስፋ ኒውስ” ከተባለ የታወቀው የሻዕቢያ ድረገጽና ዩ ቱብ ከተለጠፈው ያገኘሁት።

Eritrea, Haile Durus own Words, Adhanom Intro 2001 P1 https://youtu.be/H0s2BhVZ_RI

**Who wins the Ethio - Eitrea war 1998 - 2000 https://youtu.be/Gei2sSzeeMM**

**አመሰግናለሁ ጌታቸው ረዳ** (Editor Ethiopian Semay) getachre@aol.com